# የሶሻሊስት ኢትዮጵያ የሥራ ክንውኖች

# በመሠረታዊ ሕጎች እንደታየው ።

በፋሲል ናሆም *

## አብዮቱ ፤ ወሳኝ ወቅትነቱ ።

ኢትዮጵያ በዓለም ውስጥ ጥንታዊ ከሆኑት አገሮች አንዷ ናት ። ከክርስቶስ ልደት በፊት ከብዙ ምዕተ ዓመታት ጀምሮ አስደናቂና ያልተቋረጠ የነፃነት ታሪክ ይዛ የቆየች አገር ናት ።[1] ስለዚህም ከቅኝ አገዛዝ መንጋጋ በሃይል በመላቀቅ በጣም በቅርብ ጊዜ ሕልውናቸውን ከአገኙት ከአብዛኞዎቹ የአፍሪካ እና ሌሎች ታዳጊ አገሮች መካከል ጎላ ብላ ትታያለች ። በሌላው ረገድ ግን ፥ ኢትዮጵያ ገና በማደግ ላይ ያለች ሀገር ናት ፤ በዚህም የተነሳ የታዳጊ አገሮች ልዩ ምልክት የሆነውን አስከፊ የሶስዮ ኢኮኖሚ ኋላ ቀርነት አብራ ተካፍላለች ። ኢትዮጵያ ረዘም ያለ የነፃነት ታሪክ ፥ ኩሩና ወኔ ያለው ሕዝብና ገና ያልተነካ ሰፊ የተፈጥሮ ሀብት ቢኖራትም ፤ ባለመታደል እስከአሁን ድረስ ሕዝቦችዋ በድህነትና በኋላ ቀርነት የሚማቅቁበት አገር ሆና መቆየቷ ነው ። በኢትዮጵያ ሕዝብ ላይ ለረጅም ጊዜ እንደ ቀንበር ሆኖ ሲያስጨንቀው የቆየው የፊውዳሉ ሥርዓት ፥ መንግሥታዊ መዋቅሩና አስተዳደሩ በመሠረቱ ይህን ለመሰለው ሁኔታ ተጠያቂ ነው ። እንግዲህ ለብዙ ጊዜ የተጠበቀውን ሕዝባዊ አብዮት መፈንዳት ዋነኛ ምክንያት የሆነው ይህ ሁኔታ ነበር ።

ሕዝባዊ አብዮት አንድ ጊዜ ብቻ የሚፈጸም ድርጊት ወይም ሁኔታ አይደለም ፤ ረዥምና አስቸጋሪ የሆነ ሂደት እንጂ ። ይህ አብዮት ከቅርብ ጊዜ ወዲህ በተለይም በ፲፱፻፷፮ና በ፲፱፻፷፯ ዓ/ም መካከል ባሉት ዓመታት ውስጥ በሠርቶ አደሩ ፥ በወታደሩ ፥ በአርሶ አደሩ ፥ በተማሪውና በምሁሩ የለውጥ ፍላጎት ምክንያት በተደረጉት ትግሎች አያሌ ያለፉ ታሪኮች አሉት ። ይህም ጽሑፍ በሚዘጋጅበት ጊዜ የአብዮቱ ሂደት ገና በመጀመሪያ ገጽታው ላይ ስለሆነ የአብዮቱን ውጤቶች በትክክል ለመገምገምና ለመጨበጥ በቂ ጊዜ አይደለም ። ይሁንና ፥ በዚህ የመጀመሪያ ገጽታም ቢሆን ፍጹም መሠረታዊ የሆኑ የሥራ ክንውኖች ጎልተው ይታያሉ ። የዚህችም አጭር መቅድማዊ ጽሑፍ ዓላማ ባለፉት ዓመታት ውስጥ የአብዮቱ ዋና ዋና የሥራ ክንውኖች በመሠረታዊ ሕጎች ውስጥ እንዴት እንደተፈነጠቁ ለማየት እንጂ ዝርዝርና ጥልቅ ትንተና ለማድረግ አይደለም ።

የኢትዮጵያ አብዮት "የሕግ አብዮት" በመሆኑ ፥ በአብዮቱ ሂደት ውስጥ የተፈጸሙትን ዋነኞቹን የኢትዮጵያን የሥራ ክንውኖች ፥ የወጡትን መሠረታዊ ሕጎች በመመርመር ከሞላ ጎደል ትክክለኛ መልካቸውን ማቅረብ ይቻላል ። "የሕግ አብዮት" የሚለውን ሐረግ በዚህ ጽሑፍ ውስጥ እንዴት እንደተጠቀምንበት በአጭሩ መግለጽ ያስፈልግ ይሆናል ። ይኸውም ሁለት ትርጉም ያዘለ ነው ። መጀመሪያ "የሕግ አብዮት" የሚለው ሐረግ ቴክኒካዊ አገላለጽ ነው ። ይህም ማለት የኢትዮጵያ አብዮት አንዱ መለያ ጠባዩ መሠረታዊ ለውጦችን ለማምጣት በሕግ መጠቀሙ ነው ። እስካሁን የተደረጉት መሠረታዊ ለውጦች ሁሉ አግባብ ያለው ሕግ ተመክሮበት ሳይወጣ ወይም ሳይታወጅ አልተፈጸሙም ።[2] ይሁንና "የሕግ አብዮት" የሚለው ሐረግ በዚህ ጽሑፍ ውስጥ የተሰጠው ሁለተኛው ትርጉም ጥልቅ የሆነ ፍሬ ነገር ያዘለ ነው ። ይኸውም አብዮቱ አብዛኛውን ፊውዳላዊ በነበረው የኑሮ ሥርዓት ውስጥ ሲከማች በቆየው አጠቃላይ ጭቆናና በደል ላይ የተመሠረተ ፍንዳታ ነበር ። ዓላማውም አዲስ ፍትሕን ለመቀዳጀት ነው ። ፍትሕ ሲባልም ውሉን ከሆነው ከግለሰብ አንጻር የሚታይ ሳይሆን ፥ ለጥቂቶቹ የከፍተኛው መደብ አባላት ልዩ መብት ማጎናጸፊያም ሳይሆን ፥ ሥርዓትን በተከተለና ሰፋ ባለ አስተሳሰብ ፥ ፍትሕ ለሰፊው ሕዝብ በሚል አንፃር እንጂ ። ዓላማቸው ብዝበዛና ጭቆና የሆኑትን የቀድሞ ግንኙነቶችን በመለወጥ የሰውን ልጅ ማንነት በሚያረጋግጡ ሰብአዊ ግንኙነቶች በመተካት እውነተኛውን ማህበራዊ ፍትሕ በማስገኘት ነው ። ይህ ማኅበራዊ ፍትሕ አዲስ የሆነና ከቀድሞ ሁኔታ የተላቀቀ ግለሰባዊ ፍትሕ ጭምር ማስገኘቱ አይጠረጠርም ። ሕግ ልዕልናን በሚቀዳጅበት በማንኛውም በከፍተኛ ደረጃው በተለይም የሕብረተሰባዊ ሕጋዊነት ፥ (ሶሻሊስት ሌጋሊቲ) ፥ ሁል ጊዜ የሚያልመው ከፍተኛውንና ከሁሉም ይበልጥ

---

* ዲንና ረዳት ፕሮፌሰር ፥ ሕግ ፋኩልቲ ፥ አዲስ አበባ ዩኒቨርስቲ ።

1 ስለ ኢትዮጵያ ታሪክ ከተጻፉት መጻሕፍት በጥቂቱ እነዚህን መመልከት ይቻላል ። ኮንቲ ሮሲኒ ስቶሪአ ደ ኢትዮፒያ (ሮማ ፲፱፻፳፰ እ ኤ አ) ፥ ጃን ዶረስ ሲቲዮፒ (ፓሪስ ፲፱፻፶፰ እ ኤ አ የእንግሊዝኛ ትርጉም ፲፱፻፶፱ እ ኤ አ) ፥ ኤ ደብልዩ ባድጂ ኤ ሂስቶሪ ኦፍ ኢትዮፒያ ኑቢያ ኤንድ አቢሲኒያ (ጥራዝ ሁለት ለንደን ፲፱፻፳፫ እ ኤ አ) ። በተለይ ደግሞ ኤስ ሩበንሰን ዘ ሰርቫይቫል ኦፍ ኢትዮፒያን ኢንዲፐንደንስ (ለንደን ፲፱፻፸፮ እ ኤ አ) ፥ ማኅተመ ሥላሴ ወ/መስቀል ዝክረ ነገር (አዲስ አበባ ፲፱፻፵፩ እ ኤ አ) እና ተክለጻድቅ መኩሪያ የኢትዮጵያ ታሪክ ከአጼ ልብነ ድንግል እስከ አጼ ቴዎድሮስ (አዲስ አበባ ፲፱፻፶፮ እ ኤ አ ) መመልከት ይቻላል ።

2 ሕጋዊ በሆኑ ዘዴዎች ብቻ በመጠቀም አጼአዊውን ሕገ መንግሥታዊ ተቋም በተለይ በመጀመሪያው ወቅት ወደ ህብረተሰብአዊ ተቋም ማዛወር እንዳልተቻለ ግልጽ ነው ። ይህም የሆነበት ምክንያት የሥልጣን አያያዙ በማይነቃነቅ ሁኔታ ታስሮ ስለ ነበር ነው ።

የተሟላውን ፍትሕ ለማግኘት በመሆኑ ሁለቱ ማለትም ሕግና ፍትሕ በቲዎሪ የተሳሰሩ ናቸው ። የኢትዮጵያን አብዮት እንደ "የሕግ አብዮት" የቆጠርነውም በዚሁ ምክንያት ነው ። አብዮቱ የኢትዮጵያን ሰፊ ሕዝብ የኑሮ ሁኔታ ማሻሻልና ይህንንም ለማስፈጸም የሚያስችሉ ውሳኔዎች ለመስጠት አመች የሆኑ ዘዴዎችን ለመፍጠር ዓላማ ያላቸው መመሪያዎች እንዲወጡ አስችሏል ። እነዚህም የተከናወኑት በመሠረታዊ ሕጎች አማካይነት ነው ። እነዚህም መሠረታዊ ሕጎች የኢትዮጵያ ሰፊ ሕዝብ ፍላጎት እንዲገልጹ ፣ ሕብረተሰብአዊ አስተዳደር ግቡን ይመታ ዘንድ ማኅበራዊ ግንኙነቶችን እንዲቆጣጠሩ ፣ ብሎም የኢትዮጵያ የማኅበራዊና የመንግሥታዊ ሥርዓት መሠረቶች እንዲሆኑ የታሰቡ የሕግ መሠረታዊ አሳቦች ድምር ውጤት ናቸው ።

'መሠረታዊ ሕጎች' ሲባል በአንዳንድ ሰዎች አእምሮ ውስጥ የሕገ መንግሥትን ሀሳብ ሊያሳድር ይችል ይሆናል ። የሕግ ሰዎችም በመሠረታዊ ሕጎችና በሕገ መንግሥት መካከል ስላለው ግንኙነት መመራመር ይጀምሩ ይሆናል ። ሕገ መንግሥት ሲባል የሚታሰበው እብዛኛውን ጊዜ በአንድ ጽሑፍ ተወስኖ የቀረበ የመንግሥትን መሠረታዊ መመሪያዎች የያዘ መሠረታዊ ሕግ ነው ከተባለ ፣ ኢትዮጵያ እስከአሁን ድረስ ይህን የመሰለ በአንድ ጽሑፍ የተወሰነ በኦፊሴል የጸደቀ (de jure) ሕገ መንግሥት የላትም ። ይሁን እንጂ ይህ አባባል አንድን ሰው ኢትዮጵያ ሕገ መንግሥት የላትም ወደሚለው የተሳሳተ አቅጣጫ ሊመራው አይገባም ፤ ኢትዮጵያ በአሁኑ ጊዜ ተግባራዊ (de facto) ሕገ መንግሥት አላትና ። ይህንንም የምንልበት ምክንያት ፣ ከዚህ ቀጥሎ የምንመለከታቸው ልዩ ልዩ መሠረታዊ ሕጎች ሕገ መንግሥታዊ ይዘት ያላቸው በመሆናቸው ነው ።[3]

እነዚህ መሠረታዊ ሕጎች እንደ ቅድመ ሕገ መንግሥት ሕገ መንግሥታዊ ደንቦች (constitutional acts) መታሰብ ይኖርባቸዋል ። ከዚህም በላይ እነዚሁኑ ከሁለት ቦታ መክፈሉ ተገቢና አመቺም ነው ። የመጀመሪያዎቹ ዓይነቶች ጊዜያዊ ሕገ መንግሥታዊ ደንቦች (provisional constitutional acts) ናቸው ። እነዚህም የቀድሞ ያረጀ ያፈጀ ሕገ መንግሥታዊ ሥርዓት ለማስወገድና አዲስ ሕገ መንግሥታዊ መመሪያዎችን ፣ እንዲሁም አዲስ የውሳኔ አሰጣጥና የሥነ ሥርዓት ጥርጊያ መንገዶችን ለማውጣት ሲባል ሆን ተብሎ የታወጁ ጊዜያዊ ፣ ክፍት ቦታን የሚያሟሉ ፣ ሕገ መንግሥታዊ ደንቦች ናቸው ። እነርሱም በተፈጥሮአቸው ጊዜያዊ በመሆናቸው በኦፊሴል የፀደቀ (de jure) ሕገ መንግሥት የሚያስፈልግበት የፖለቲካ ወቅት ሲደርስ አዲስ ሕብረተሰብአዊ ሕገ መንግሥት ይተካቸዋል ። ስለዚህ እነዚህን ጊዜያዊ ሕገ መንግሥታዊ ደንቦች በዚህ ጽሑፍ ውስጥ እንመለከታቸውም ። እዚህ ላይ የ፲፱፻፷፮ አዋጅ ቁጥር ፩ እና ተከታታይ ማሻሻያዎቹ የጊዜያዊ ሕገ መንግሥታዊ ደንቦች ጥሩ ምሳሌዎች መሆናቸውን ማስታወሱ ብቻ ይበቃል ።[4]

ሁለተኛዎቹ ዓይነቶች ይበልጥ ቀዋሚና መሠረታዊ የሆኑ ሕገ መንግሥታዊ ደንቦች ናቸው ። እነዚህን ደንቦች እንደ ቀዋሚ ሕገ መንግሥታዊ ደንቦች መቁጠር ዋነኛና (substantive) ሥነ ሥርዓታዊ ሕጎችን በሚመለከት ረገድ ተጨማሪ ዕድገትና ለውጥ አይኖርም ማለት አይደለም ። ነገር ግን አዲሱ ሕብረተሰብአዊ ሕገ መንግሥት በቀዋሚ ሕገ መንግሥታዊ ደንቦች ውስጥ ያሉት መሠረታዊ መመሪያዎች እንዲጠናከሩና በከፍተኛ ጥንቃቄ እንዲጠበቁ ያደርጋል ። በዚህ ጽሑፍም ትኩረት የሚሰጠው ለነዚሁ ለሁለተኞቹ ዓይነቶች ሕገ መንግሥታዊ ደንቦች ነው ።

ለዚህም ፣ አምስት መሠረታዊ ሕጎች በሕገ መንግሥታዊ ደንቦች መደብ ውስጥ በግልጽ የሚገቡ በመሆናቸው ሆን ተብሎ ተመርጠዋል ። እነዚህም አንድ ፣ የገጠርን መሬት የሕዝብ ሀብት ለማድረግ የወጣው አዋጅ ፤ ሁለት ፣ የገበሬዎች ማህበራትን ለማደራጀትና ለማጠናከር የወጣ አዋጅ ፤ ሦስት ፣ የከተማ ቦታና ትርፍ ቤትን የመንግሥት ንብረት ለማድረግ የወጣ አዋጅ ፤ አራት ፣ የከተማ ነዋሪዎች የህብረት ሥራ ማህበር ማጠናከሪያ የማዘጋጃ ቤቶች አዋጅና ፤ አምስት ፣ የሠራተኛ ጉዳይ አዋጅ ናቸው ።

## የገጠሩ መለወጥ ።

በአንዳንድ የምሁራን አካባቢዎች ስለ "መሬት ይዞታ መሻሻልና" ስለ "መሬት ይዞታ ማሻሻያ ሕጎች" በሚነገርበት ጊዜ የመሬት ይዞታ ለውጥ የመጠን ለውጥ ብቻ ይመስል ፣ መሠረታዊ የዓይነት ለውጥ መኖሩን በመዘንጋት ፣ የተለያዩ ሕብረተሰቦች ያገኙአቸውን የመሬት ይዞታ ለውጥ ልምዶች አቀላቅሎ ማየት የተለመደ ነው ። የገጠርን መሬት የሕዝብ ለማድረግ የወጣውን አዋጅ[5] እንደ መሬት ይዞታ ማሻሻያ አዋጅ ብቻ መቁጠር ያልሆነ ስም መስጠት ብቻ ሳይሆን ፣ የአዋጁን ቁም ነገር መናቅና የሰጠውን አገልግሎት መርሳት ይሆናል ። አዋጁ የሚደነግገው ጥገናዊ ለውጥን ሳይሆን የቀድሞውን የገጠሩን ሥርዓት ፍጹም መለወጥ ነው ። አዋጁ[5] ከአዲስ መሠረት በመነሳት በአዲስ የታሪክ ገጽ ላይ እንድንጀምር ያደርጋል ። እንግዲህ ይህ አዋጅ ያለ ጥርጥር የአብዮቱ ወሳኝ ገጽ በመሆኑ ፣ አብዮቱ ከወለዳቸው በጣም መሠረታዊ ከሆኑት ሕገ መንግስታዊ ደንቦች መካከል አውራ ሆኖ ሊታይ ይገባል ።

ይህ አዋጅ የገጠርን መሬት የሕዝብ ሀብት በማድረግና የፊውዳሉን የምርት ግንኙነቶች ፈጽሞ በማቋ

3 ከመሠረታውያን ሕጎች ሌላ መሠረታውያን የሆኑ የፖሊሲ መግለጫዎች እንዳሉ መዘንጋት አያስፈልግም ። ከወጡት መግለጫዎች ከፍተኛው ብሔራዊ ዲሞክራሲያዊ አብዮታዊው መለስተኛ ፕሮግራም ነው ። ይህ መግለጫ ለአብዮቱ እጠቃላይ መመሪያ ቢሆንም ፣ ከዚህ ማለትም ስለመሠረታዊ ሕጎች ብቻ ከሚያወሳ ጽሑፍ ወጣ ብሎ ይገኛል ።

4 ጊዜያዊ ወታደራዊ መንግሥትን የተቋቋመበት አዋጅ ቁ ፩ የ፲፱፻፷፮ ዓ/ም ነጋሪት ጋዜጣ ፴፬ኛው ዓመት ቁጥር ፩ ። ይህ አዋጅና ማሻሻያዎቹ በጊዜያዊ ወታደራዊ አስተዳደር ደርግና የሚኒስትሮች ምክር ቤትን ሥልጣንና ኃላፊነት እንደገና ለመወሰን በወጣው አዋጅ ቁ ፩፻፲ የ፲፱፻፷፱ ዓ/ም ነጋሪት ጋዜጣ ፴፮ኛ ዓመት ቁጥር ፲፫ ተጠቃልሎአል ።

5 የገጠር መሬት የሕዝብ ሀብት ለማድረግ የወጣ አዋጅ ቁ ፴፩ የ፲፱፻፷፯ ዓ/ም ነጋሪት ጋዜጣ ፴፬ ዓመት ቁ ፳፮ ።

ረጥ የፊውዳሉን መዋቅር ከመሠረቱ በመምታት ለወደፊቱ እንዳይንሰራራ አድርጎታል ። በገጠሪቱ ኢትዮጵያ ለመሬት የሚሰጠው ክብርና ከፍተኛ ግምት በቀላሉ የሚታይ አይደለም ። በአዋጁ መግቢያ ላይ እንደ ተመለከተው "እንድ ሰው በህብረተሰቡ ውስጥ ሊኖረው የሚችለው የኑሮ ደረጃ ፣ መብት እንዲሁም ክብርና ማዕረግ የሚወሰነው ከመሬት ጋር ባለው ግንኙነት" ነው ። ከዚህም በላይ ገጠሩ የኢትዮጵያ ክፍል ከመቶ ዘጠና የሚሆነውን የኢትዮጵያን አካል ስለሚያጠቃልል በትክክል ዋነኛው ኢትዮጵያ ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል ።

እዚህ ላይ ነው የፊውዳሉ ሥርዓት ሥረ መሠረቱ ፣ ሰውን በሰው መበዝበዝ ላይ የተመሠረተው የእርሻ ኤኮኖሚ ፣ በጣም ጥቂት በነበሩ ግለሰቦች እጅ የነበረውና ከትውልድ ሲተላለፍ የቆየው የመሬት የግል ባለ ሀብትነት ፣ እንዲሁም በኤኮኖሚ ፣ በማኅበራዊና በፖለቲካ መስክ በሰፊው ሕዝብ ላይ የሚደርሰው በደል በዘዴ እንዲስፋፋ ያደረገው ። ስለዚህ ነው በተወላሰበ መንገድ የተደራረበውና ብዙ መልኮች ያሉት የጭሰኛውና የባላባቱ ግንኙነቶች ባጠቃላይም በእርሻው መስክ የነበረውን ግንኙነት መመታትና ፈጽሞ መለወጥ የነበረበት ። የአዋጁ መግቢያ በግልጽ እንደሚያስረዳው የተፈለገው የፊውዳሉን የመሬት ይዞታ ሥርዓት ሙሉ በሙሉ መደምሰስና በቦታውም አዲስ ሥርዓት መተካት ነው ። ይህ አዲስ ሥርዓት ሰፋ ያለ የኤኮኖሚ ፣ የማኅበራዊና የፖለቲካ ውጤት ይኖረዋል ። ለትክክለኛ የመሬት ድልድል ፣ ለገጠሩ ሕዝብ አስተማማኝ ሥራ ለማስገኘት ፣ በፊውዳሉ ሥርዓት ታፍኖ የነበረውን የሰው ጉልበት ወደ ኢንዱስትሪው ክፍለ ኤኮኖሚ እንዲሰማራ ለማድረግ ፣ የራስን በራስ አስተዳደር ለመመስረትና በዚህም ማኅበራዊ ፍትሕን የሚያስገኝ ሥርዓት ለመገንባት መሠረት ይሆናል ።

እነዚህን ግቦች ለመምታት የተወሰዱት እርምጃዎች ቀጥተኛ ነበሩ ። ከዚህ እንደሚከተለውም ባጭሩ እንጠቅሳቸዋለን ፡

እንደኛ ፤ ከየካቲት ፳፮ ቀን ፲፱፻፷፯ ዓ/ም ጀምሮ የገጠር መሬት ሁሉ የኢትዮጵያ ሕዝብ የጋራ ንብረት እንዲሆን ተደረገ ።[6] በሌላ አነጋገር ከዚህ ጊዜ ጀምሮ የመሬት የግል ንብረትነት በመቅረቱ ማንኛውም ሰው ወይም ድርጅት የገጠርን መሬት ለመግዛት ፣ ለመሸጥ ወይም ለማስተላለፍ መብት አይኖረውም ማለት ነው ። ሁለተኛ ፤ የገጠር መሬት በዘር ፣ በጾታ ፣ በቋንቋና በሃይማኖት ምንም ልዩነት ሳይደረግ በግሉ ለማረስ ፈቃደኛ ለሆነ ለማንኛውም ኢትዮጵያዊ ሁሉ በይዞታ እንዲከፋፈል ተደነገገ ። በይዞታ የሚመደበው መሬት በተቻለ መጠን እኩል እንዲሆን ከመደረጉም በላይ በማንኛቸውም ጊዜ ከ፲ ሄክታር እንዳይበልጥና የይዞታው መጠን እንደአካባቢው ሁናቴና እንደመሬቱ ለምነት እንዲወሰን ተደረገ[7] ። ሦስተኛ ፤ አዋጁን በሥራ የመተርጎሙ ተግባር በየ፰፻ ሄክታር ክልል ውስጥና እንዲሁም በወረዳና በአውራጃ ደረጃ ለተቋቋሙት የገበሬ ማህበራት ተሰጠ ።[8]

የገጠርን መሬት የሕዝብ ሀብት ለማድረግ የወጣው አዋጅ በዚህ ጽሑፍ ውስጥ መገለጽ የማያስፈልጋቸውን በግል ባለሀብትነት ያልተያዙት የወል ርስቱና የዘላን መሬቶችን የሚመለከቱ የሕግ አንቀጾችን ጨምሮ ልዩ ልዩ ዝርዝር ዘዴዎች አቅርቧል ።[9] ማህበራትን የማቋቋም ኃላፊነት ለእርሻና ሕዝብ ማስፈር ሚኒስቴር (የዛሬው ግብርና ሚኒስቴር) ከአገር አስተዳደር ሚኒስቴር ጋር በመተባበር እንዲሠራ የተሰጠ መሆኑን መጥቀሱ በቂ ነው ።[10]

የገበሬ ማህበራትን በሚመለከት ረገድ ሕገ መንግሥታዊ ትኩረት የሚሰጠውና ከገጠር መሬት አዋጅ ጋር የቅርብ ግንኙነት ያለው ሌላው ሕግ በታኅሣሥ ወር ፲፱፻፷፷ ዓ/ም የወጣው ፣ የገበሬዎች ማህበራት ማደራጃና ማጠናከሪያ አዋጅ ነው ።[11] እርእስቱ ራሱ እንደሚያመለክተው አዋጁ ለገበሬዎች ማህበራት ተጨማሪ ሀልውና የሚሰጥና የሚያጠናክራቸው ነው ። አዋጁ በተጨማሪም የአገልግሎት የህብረት ሥራ ማህበራትን ፣ የአምራቾች የህብረት እርሻ ሥራ ማህበራትን ፣ የሴቶች ማህበራትንና የገበሬዎች ጥበቃ ጓዶችን ያቋቁማል ። ከዚህም በላይ አዋጁ ስለገበሬዎች ማህበራት የፍርድ ሸንጎዎች ሰፋ ባለ ሁኔታ ይዘረዝራል ፡ የገበሬዎች ማህበራት የፍርድ ሸንጎዎች የገጠርን መሬት የሕዝብ ሀብት ባደረገው አዋጅ ቀደም ብለው ተቋቁመዋል ። አዲስም ሆነ በቀጠሮ ላይ የነበሩትን የመሬት ክርክሮች የመዳኘቱ ተግባር ከመደበኛ ፍርድ ቤቶች ሥልጣን ውጭ ተደርጎ በወረዳና በአውራጃ ደረጃ ለሚገኙት የገበሬ ማህበራት የፍርድ ሸንጎዎች ተሰጥቷል ።

የህብረት ሥራ ማህበራትን በየደረጃው ማቋቋምና ማስፋፋት የተፈለገው እርሶ አደሩ በጋራ ከመሥራት የሚመነጩትን ጥቅሞች የሚያገኝበትን የህብረተሰብአዊ እርሻን መሠረት ለመጣል ታስቦ ነው ።[12] እንግዲህ የህብረት ሥራ ማህበራት ተቋም በማህበራዊ ፣ በኤኮኖሚና በፖለቲካ መስኮች ከፍተኛ ቦታ ይዞ ይገኛል ። በዓይነታቸው የሚለያዩትንና በልዩ ልዩ የሥልጣን ደረጃ የሚገኙትን የህብረት ሥራ ማህበራት የማስተዳደሩ ሥራ በአርሶ አደሩ እጅ የሚገኝ በመሆኑ እነዚህ ተቋሞች የኤኮኖሚ እድገት ማግኛ መንገዶች መሆናቸው ብቻ ሳይሆን ፣ የመማሪያ ፣ ራስን በራስ የማስተዳደሪያና የአካባቢን ችግር የመፍቻ ፣ በልማት እንቅስቃሴዎች የመሳተፊያ ትምህርት ቤቶች በመሆን በተጨማሪ የሚያገለግሉ መሆናቸውም መጠቀስ ይገባዋል ።

6 የገጠር መሬት አዋጅ አንቀጽ ፫ (፩-፪) ።
7 የገጠር መሬት አዋጅ አንቀጽ ፬ ።
8 የገጠር መሬት አዋጅ አንቀጽ ፰ እስከ ፲፭ ።
9 የገጠር መሬት አዋጅ አንቀጽ ፲፱ እስከ ፳፮ ።
10 የገጠር መሬት አዋጅ አንቀጽ ፲፯ ።
11 የገበሬ ማህበራት ለማቋቋምና ለማጠናከር የወጣ አዋጅ ቁጥር ፸፮ የ፲፱፻፷፱ ዓ/ም ነጋሪት ጋዜጣ ፴፮ኛ ዓመት ቁ ፲፭ ።
12 የገበሬ ማህበራት አዋጅ አንቀጽ ፯ እና ፰ ።

የሴቶች ማህበራት መቋቋም በአብዮቱ ውስጥ የሴቶች የተደራጀ ተሳትፎ ለህብረተሰብአዊ ድል ፍጹም አስፈላጊ መሆኑን በመገንዘብ ላይ የተመሠረተ ነው ። ሴቶች በኢትዮጵያ ህብረተሰብ ውስጥ ረዘም ላለ ጊዜ ሁለተኛ ደረጃ ዜጋ ሆነው ቆይተዋል ። እንዲህ ያለው ሁኔታም መቃናት ብቻ ሳይሆን ጨርሶ መለወጥ አለበት ። ሴቶች እንደወንዶች በአገሪቱ የፖለቲካ ፣ የኤኮኖሚና የሶሻል እድገት ውስጥ በእኩል የመታየት መብት ሊኖራቸው ይገባል በሕግ የሰውነት መብት እንዲሁም ሰፋ ያለ ሥልጣንና ተግባር ያለው የሴቶች ማህበርን ማቋቋም በአንድ አብዮት ውስጥ ያለ የአንድ ማኅበራዊ ለውጥ ሂደት ዓይነተኛ ምልክቱ ነው ።

በመጨረሻም የገበሬዎች ማህበራት አዋጅ ገበሬዎችንና የገበሬዎችን ማህበራት ፣ እንዲሁም አብዮቱንና የወደፊት እድገቱንም ጭምር ለመጠበቅ የሚያስችሉ የጥበቃ ጓዶችን ያቋቁማል ። የጥበቃ ጓዶችም የየራሳቸውን አካባቢ የመጠበቅ ግዴታ አለባቸው ። የጥበቃ ጓዶች በተጨማሪም የሕዝባዊ ጦር (ሚሊሺያ) አስኳል ናቸው ፤ ስለሆነም አብዮቱን ከውስጥና ከውጭ ጠላቶች የመጠበቅ ከፍተኛ ኃላፊነት ተጥሎባቸዋል ።

## የከተማው መለወጥ ።

ሕገ መንግሥታዊ ትኩረት የሚሰጠው ሌላው ሕግ የከተማን ቦታና ትርፍ ቤት የመንግሥት ንብረት ለማድረግ ሐምሌ ፲፱፻፷፯ ዓ/ም የወጣው አዋጅ ነው ።[13] ይህ አዋጅ የገጠርን መሬት ለሕዝብ ያደረገው አዋጅ ጓደኛና ማሟያ ነው ። የገጠር መሬት አዋጅ በፊውዳሉና በበዝባዡ የገጠር ግንኙነት ላይ ያስከተለውን መሠረታዊ ለውጥ ሁሉ ይህም አዋጅ በከተማው የፊውዳልና የበዝባዥ ግንኙነት ላይ አስከትለዋል ። አዋጁ ከጸናበት ቀን ጀምሮ የከተማ ቦታ የመንግሥት ሀብት ሆኗል ።[14] ስለዚህም የከተማ ቦታ የግል ንብረትነቱ በማክተሙ ማንኛውም ሰው ወይም ድርጅት የከተማን ቦታ የመግዛት ፤ የመሸጥ ወይም የመለወጥ መብት እንዳይኖረው ያደርጋል ። አዋጁ በመሬት ከበርቴና ጭሰኛ መካከል የነበረውን ግንኙነት ያጠፋል ። በተጨማሪም አዋጁ የኢትዮጵያ ዜጎች ለሆኑ ሁሉ የመኖሪያ ቤቶችን መሥሪያ የሚሆን እስከ ፭፻ ካሬ ሜትር የሚደርስ የከተማ ቦታ ፣ እንዲሁም በሚፈለገው መጠን ለመሥሪያ ቤት የሚሆን የከተማ ቦታ የይዞታው መብት ለመስጠት እንዲቻል አግባብ ላለው የሚኒስቴር መሥሪያ ቤት ሥልጣን ይሰጣል ።[15]

ቤቶችን በሚመለከት ረገድ ማንኛውም ሰው ወይም ቤተሰብ ከአንድ መኖሪያ ቤት በላይ በባለቤትነት እንዳይዝ ተከልክሎ ማናቸውም ትርፍ ቤቶች ሁሉ ወዲያውኑ ወደ መንግሥት እጅ እንዲዛወሩ ተደርገዋል ።[16] ከዚህም በላይ የመኖሪያና የመሥሪያ ቤቶችን ለማከራየት መብት ያለው አካል መንግሥት ብቻ መሆኑን የቤት ኪራዮችም በግል ጥቅም ላይ በተመሠረተው አኳኋን ሳይሆን በቴክኒካዊ ግምት ይወሰናሉ ።[17]

አዋጁ የከተማ ነዋሪዎች የህብረት ሥራ ማህበራትን ያቋቁማል ። ይህም በመስከረም ፲፱፻፷፱ ዓ/ም ወደ ታወጀው የከተማ ነዋሪዎች የኅብረት ሥራ ማህበራት ማጠናከሪያና የማዘጋጃ ቤቶች አዋጅ ያመጣናል ።[18] አዋጁ በየደረጃው የተቋቋሙትን የከተማ ነዋሪዎች ማህበራት የሕግ ሰውነት እንዲኖራቸው ያደርጋል ። በተጨማሪም አዋጁ የከተማ ነዋሪዎችን ጉዳይ በማስፈጸም እንዲሁም አብዮቱን በመጠበቅና በማጠናከር ረገድ ለቀበሌ ፣ ለከፍተኛና ለአጠቃላይ የከተማ ነዋሪዎች ማህበራት ከፍ ያለ ሥልጣንና ተግባር ይሰጣል ። የከተማ ነዋሪዎች ማህበራትም የፖሊሲ አውጭ ኮሚቴዎች የሕዝብ ደህንነት ኮሚቴዎችና የፍርድ ሸንጎዎችን ያቋቁማሉ ።[19] የፖሊሲ አውጭ ኮሚቴዎች የከተማ ነዋሪዎችንና የአብዮቱን ጥቅም ለመጠበቅና ለማራመድ የሚያስችሉ አጠቃላይ የአስተዳደር ሥልጣኖች አሏቸው ። የሕዝብ ደህንነት ኮሚቴዎች የየአካባቢያቸውን ጸጥታ መጠበቅ ብቻ ሳይሆን የሕዝባዊ ጦር አባሎች ሊመለመሉ የሚችሉባቸው ምንጮች በመሆን ያገለግላሉ ። የፍርድ ሸንጎዎች የከተማ ቦታና ቤቶችን በሚመለከት ረገድ የሚነሱ ክርክሮችን እንዲሁም አነስተኛ የፍትሐ ብሔር ጉዳዮችንና ቀላል ጥፋቶችን በዳኝነት ያያሉ ።[20] ጉዳዩ የሚመለከተው የሚኒስቴር መሥሪያ ቤት ከአጠቃላይ የማዘጋጃ ቤት ባለሥልጣኖች ጋር በመተባበር ለከተማ ነዋሪዎች ማህበራት ሥራ አስፈላጊ መመሪያዎችን ይሰጣል ፤ ሥራቸውንም ይቆጣጠራል ።

## የሠራተኛ ጉዳይን በሚመለከት ረገድ የተደረገ ለውጥ ።

ልንመለከተው የሚገባ የመጨረሻው መሠረታዊ ሕግ በኅዳር ወር ፲፱፻፷፰ ዓ/ም የወጣው የሠራተኛ ጉዳይ አዋጅ ነው ።[21] ይህ አዋጅ የኅብረተሰብአዊ የሶሻልና የኤኮኖሚ ዋና ዋና መሠረታዊ አሳቦችን ያረጋግጣል ፤ የሠራተኛውንም መብቶችና የሥራ ሁኔታዎች በሚገባ ለመጠበቅ የሚያስችሉትን ሕጋዊ መዋቅሮች ይፈጥራል የአዋጁ መግቢያ "ሥራ ለሰው ልጅ ክብሩ ነው" በማለት መሠረታዊ መመሪያ ደንግጓልናል ፤ እንዲሁም በማያወላውል አኳኋን ማንኛውም ግለሰብ "የመሥራት መብትም ሆነ ግዴታ" እንዳለው ያስገነዝባል ። አዋጁ ሠራተኛውን የምርት ሁሉ ምንጭና መሠረት አድርጎ ይመለከተዋል ፤ ስለዚህም ከብዝበዛ ነፃ በመውጣት ደኅንነቱንና ጤንነቱን በትክክል በመጠበቅ ፣ እንዲሁም ትክክለኛ ክፍያ ማግኘቱን በማረ

13 የከተማ ቦታና ትርፍ ቤት የመንግሥት ንብረት ለማድረግ የወጣ አዋጅ ቁ ፵፯ ፲፱፻፷፯ ዓ/ም ነጋሪት ጋዜጣ ፴፬ኛ ዓመት ቁጥር ፵፩ ።
14 የከተማ ቦታ አዋጅ አንቀጽ ፫ ።
15 የከተማ ቦታ አዋጅ አንቀጽ ፮ ።
16 የከተማ ቦታ አዋጅ አንቀጽ ፲፩ ።
17 የከተማ ቦታ አዋጅ አንቀጽ ፳ ።
18 የከተማ ነዋሪዎች ማህበራት ማጠናከሪያና የማዘጋጃ ቤቶች አዋጅ ቁጥር ፩፻፬ የ፲፱፻፷፱ ዓ/ም ነጋሪት ጋዜጣ ፴፭ኛ ዓመት ቁ ፭ ።
19 የከተማ ነዋሪዎች ማህበራት አዋጅ አንቀጽ ፲ ።
20 የከተማ ነዋሪዎች ማህበራት አዋጅ አንቀጽ ፲፩ ።
21 የሠራተኛ ጉዳይ አዋጅ ቁጥር ፷፬ የ፲፱፻፷፰ ዓ/ም ነጋሪት ጋዜጣ ፴፭ኛ ዓመት ቁ ፲፩ ።

ጋገጥ የሠራተኛውን የኑሮ ደረጃ ማሻሻል ወሳኝ ነው ብሎ ይቆጥራል ። በተጨማሪም ለእያንዳንዱ ኢትዮጵያዊ በዘር ፤ በጎሣ ፣ በጾታና በሃይማኖት ምንም ልዩነት ሳይደረግ እኩል የሥራ ዕድል እንደሚሰጥ ይደነግጋል ። ይህንንም ለማድረግ አዋጁ የሥራ ዕድሎችን በማስፋፋትና የሥራ ፈትነት ችግሮችን በማስወገድ ዓላማ የተመሠረተ ስለ አገሪቱ የሰው ኃይል መጠንና ሙሉ አጠቃቀም ጥናት ማካሄድ አስፈላጊ መሆኑን ያምናል ።

አዋጁ በትክክል እንደሚያስረዳው ፣ ህብረተሰብአዊነትን መገንባትና ይህንንም ውጤት ለማስገኘት የሠራተኛውን ንቃተ ሕሊና ማሳደግ ፣ እንዲሁም ሠራተኛውን በአገሪቱ ዕድገት ውስጥ ሙሉ በሙሉ ተሳታፊ እንዲሆን ማድረግ አስፈላጊ ነው ። አዋጁ የሚደነግጋቸው መሠረታዊ ዓላማዎች ሊገኙ የሚችሉት ሠራተኞች በየሙያ ማኅበሮቻቸው ሲደራጁና የህብረተሰባዊ መመሪያዎችን መስመር በመከተል ተግባሮቻቸውን በሥነ ሥርዓት ሲከታተሉ ብቻ ነው ። የሞያ ማህበራት በልዩ ልዩ ደረጃ ሥልጣን ተሰጥቶአቸው የተቋቋሙ ዲሞክራሲያዊ ድርጅቶች ናቸው ። ሠራተኞች በአዋጁ እንደ ተገለጸው የሠራተኛ ማህበር አባላት መሆን ይችላሉ ። በአንድ ድርጅት ውስጥ ከ፳ ያላነሱ ሠራተኞች እስካሉ ድረስ በዚህ ድርጅት ውስጥ አንድ የሙያ ማህበር ማቋቋም ይቻላል ። ከ፳ በታች ሠራተኞች ባሏቸው ትናንሽ ድርጅቶች ውስጥ የሚገኙ ሠራተኞች ደግሞ ከሌሎች በተመሳሳይ ድርጅቶች ውስጥ ከሚሠሩ ሠራተኞች ጋር በአንድነት ሆነው ጠቅላላ ማህበርን ሊያቋቁሙ ይችላሉ ። እነዚህ በመጀመሪያ ደረጃ የሚገኙ ጠቅላላ ማህበራትና የሙያ ማህበራት በአሁኑ ጊዜ ቁጥራቸው ዘጠኝ የደረሰውን የኢንዱስትሪ ማህበራት እንዲያቋቁሙ በየኤኮኖሚ የሥራ ዘርፋቸው ይመደባሉ ። በመጨረሻም ዘጠኙ የኢንዱስትሪ ማህበራት በአንድነት ሆነው አገር አቀፍ የሆነውን መላው የኢትዮጵያ ሠራተኞች ማህበር ያቋቁማሉ ። መላው የኢትዮጵያ ሠራተኞች ማህበር በኢትዮጵያ ውስጥ የሚገኙት ሠራተኞች ሁሉ ከመወከሉም በላይ በዓለም አቀፍ የሠራተኞች ማህበራትም ውስጥ ወካይና ተጠሪ ይሆናል ።[22]

አዋጁ ሠራተኞች በአስተዳደር ሥራ እንዲሳተፉ ፣ የሥራ ቅልጥፍና እንዲጨምርና ሰላምና መተሳሰብ የተሞላበት የሥራ ግንኙነት እንዲፈጠር ባሉት ዓላማዎች መሠረት እነዚህን ዓላማዎች ከግቡ ለማድረስ የሚያስችሉትን የረቀቀ የሕግ ዘዴንና የተለያዩ ተቋሞችን ይፈጥራል ። እነዚህም ቁጥራቸው ከአሥር የማያንስ ሠራተኞች በሚገኙበት በእያንዳንዱ ድርጅት ውስጥ ከድርጅቱና ከሠራተኛው እኩል በኩል ተወካዮች ተገኝተውበት የሚቋቋመውን የሥራ ክርክር ኮሚቴን ይጨምራሉ ። እንደዚህ ያለው የሥራ ክርክር ኮሚቴ የግል የሥራ ክርክርን በሚመለከት ረገድ በመጀመሪያ ደረጃ የማየት ሥልጣን ያለው ሲሆን የውል የሥራ ክርክርን በሚመለከት ረገድ ጉዳዩ በስምምነት እንዲፈጸም የማድረግ ሚና ይጫወታል ።[23] አዋጁ በሌሎች ደረጃዎች የሠራተኛን ጉዳይ የሚመለከቱ ችሎቶች በአውራጃና በከፍተኛ ፍርድ ቤት ደረጃ ያቋቁማል ።[24] በተጨማሪም አዋጁ ስለ መሠረታዊ የሥራ ሁኔታዎች ፣ ስለህብረት ስምምነቶች ፣ ስለ ለማጅ ሠራተኛ የሥራ ውልና አቀጣጠር እንዲሁም ተገቢ ስላልሆኑ የሥራ አፈጻጸሞች በዝርዝር ይደነግጋል ።

የሠራተኛ ጉዳይ አዋጅ የሥራንና የሠራተኛን ክቡርነት በማወጁና በሥራ አማካይነት ህብረተሰብአዊነትን ለመገንባት የሚያስችሉ ዓላማዎችን በመያዙ በሕጎች ዓለም ውስጥ ሕገ መንግሥታዊ ትኩረት ይሰጠዋል ፤ ስለሆነም እንደ ሕገ መንግሥታዊ ደንብ ሊቆጠር ይችላል ።

## ከመደንገግ በሥራ ወደ መተርጎም ።

ከዚህ በላይ የመረመርናቸው መሠረታዊ ሕጎች ሁሉ ሕገ መንግሥታዊ ትኩረት የሚሰጣቸው ናቸው ። ቀደም ሲል እንደተጠቀሰው በሕግ (በአፈሴል) የጸደቀ (de jure) ሕገ መንግሥት በሚወጣበት ጊዜ እዚህ ላይ የተነጋገርንባቸውን ሕጎች መሠረተ አሳብ አዝሎ የሚወጣና በከፍተኛ ጥንቃቄም የሚያስጠብቃቸውን ይሆናል ከዚህም በላይ እነዚህ መሠረታዊ ሕጎች ለኢትዮጵያ ሰፊ ሕዝብ በጣም ጠቃሚ የሆነ "የሕግ አብዮት" ምልክት መሆናቸው ግልጽ ነው ። ይሁን እንጂ በጽሑፍ የሚገኙትን ግቦች በሥራ ለመተርጎም የሚያስችሉ ዘዴዎችን የማውጣቱ አስፈላጊነት መፍትሔ የሚያሻው አሁንም ያለና ወደፊትም ያለማቋረጥ ጥረት የምናደርግበት ተግባር ነው ። በሌላ አነጋገር በጽሑፍ የቀረቡት ዝርዝር ጉዳዮች ሁሉ ዘለቄታው በሥራ መተርጎም ይኖርባቸዋል ማለት ነው ። ዓላማዎችንና መሠረታዊ አሳቦችን በሥራ መተርጎም ቀላል ተግባር አይደለም ። አስቸጋሪ ጉዳዮችን ውጤት ለማስገኘት ፍቱን በሆነ መንገድ ፕሮብሌሞችን ተንትኖ ማየትና ውሳኔ መስጠት ያስፈልጋል ። ከዚህም በላይ እነዚህ የፕሮብሌም ትንተናዎች ፣ የሕግ አስፈጻሚው የመንግሥት ዘርፍ በልዩ ልዩ የሥልጣን ደረጃዎች ዝርዝር ደንቦች እንዲያወጣላቸው ያስፈልጋል ። ይህም ማለት ባጠቃላይ ሁኔታ የሚገኙትን ደንቦች ደምና ሕይወት መስጠት ይሆናል ። እነዚህም ብዙውን ጊዜ የሕግ ማስታወቂያ እየተባሉ ሊታወጁ ይችላሉ ። ከዚህም በኋላ ለእነዚህ ደንቦች ዝርዝር የሥራ ፕሮግራምና መመሪያ ሥነ ሥርዓት በማውጣት ዓላማዎችን በሥራ ለመተርጎም ይቻላል ። ከዚህም በላይ ይህን የመሰለው በሥራ የመተርጎሙ ተግባር ተፈላጊውን ውጤት የማያስገኙትን ፣ እንደገና መመርመር የሚያስፈልጋቸውን ችግር አዘል ሕጎች ካሉ ለመጠቆም ያስችላል ። እንግዲህ በሥራ የማዋሉ ተግባር ለሕጎች ይበልጥ መሻሻል ጠቃሚ መሣሪያ የሚሆኑ መረጃዎችን በመስጠት ሊያገለግል ይችላል ። ለዚህም አግባብ ያለው ምርምር የማያቋርጥ ሂደት በሚታይባቸው በጽሑፍ ባሉት ደንቦችና ሁኔታዎች ላይ ባጠቃላይ በማተኮር ወደ ተረጋገጠ ውሳኔና ውጤት ሊደርስ ይችላል ።

22 የሠራተኛ ጉዳይ አዋጅ አንቀጽ ፵፱ እስከ ፶፪ ።
23 የሠራተኛ ጉዳይ አዋጅ አንቀጽ ፸፱ እስከ ፹፩ ።
24 የሠራተኛ ጉዳይ አዋጅ አንቀጽ ፺፩ እስከ ፩፻ ።